# ጥናት አንድ ሶፎንያስ 1፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሶፎንያስ ትንቢቱን በተናገረበት ዘመን በእስራኤል ላይ ንጉስ ሆኖ ይገዛ የነበረው ሰው የአሞጽ ልጅ ኢዮስያስ ነበረ። እግዚአብሄር በባርያው ውስጥ ሆኖ እንደሚያደርግ የተናገራቸው ነገሮች፤ ማንኛውንም ነገር ከምድር ገጽ እንደሚያጠፋ፣ ሰውንና እንስሳን፣ የባህር ዓሳዎችንም ሁሉ እንደሚያጠፋ ሲሆን፤ በተለይም ደግሞ ክፉዎች የፍርስራሽ ክምር እንደሚሆኑም ያስጠነቅቃል።
2. የመጀመሪያዎቹ የሰማይን ሰራዊት ለማምለክ በሰገነት ላይ ወጥተው የሚሰግዱ፤ ማለትም መሉ ለሙሉ ለጣዖት የተሰጡ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ለእግዚአብሄር እየሰገዱ፤ በስሙም እየማሉ በሚልኮምም ደግሞ የሚምሉ፤ ማለትም እግዚአብሄርን በደባልነት የሚያኖሩ፤ ሲኦኑ፤ ሶስተኞቹ ደግሞ፤ እግዚአብሄርን ከመከተል ወደኋላ የሚመለሱና እግዚአብሄርን የማይፈልጉ፣ እንዲረዳቸውም የማይጠይቁ፤ ማለትም ለእግዚአብሄር በህይወታቸው ተገቢውን ሥፍራ የማይሰጡ ናቸው።
3. አጠቃላይ አውደ ምንባቡን ስንመለከት፤ እግዚአብሄር መስዋዕትን እንዳዘጋጀና እንግዶቹንም እንደለየ ሲናገር፤ ይሁዳን ለእርድ እንዳዘጋጃትና ተጋባዡም በእንባ 1፡6 ላይ እንደምናነበው ባቢሎንን ለማለት መሆኑ ትርጉም ይሰጣል። በተለይም በዚህ በቁ8 ላይ ተጠቅሰው የምናገኛቸው ሰዎች ማንነት ከሌሎች የሚለየው፤ ሁሉም ታላላቅና የከበሩ የቤተ መንግሥት ሰዎች እንደሆኑ እንመለከታለን።
4. “በዚያን ቀን” ሲል በቁ7 ላይ የተነገረውን የእግዚአብሄርን ቀን ነው። የተሰሙት ድምጾች፤ ከአሳ በር ጩኸት፣ ከአደባባይ ዋይታና፣ ከኮረብታዎችም ታላቅ ሽብር ይሰማል ነው የሚለው።
5. በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ሊቀጣቸው ያሉት ሰዎች፤ ተንደላቀው የሚኖሩ፣ ክፉ ይሁን መልካም እግዚአብሄር ምንም ዓይነት ነገር አያደርግም በማለት ቤት በመስራት፣ ወይናቸውን በመትከልና እግዚአብሄር የሚናገረውን ነገር በቸልተኛነት በመመልከት ኑሯቸውን የሚኖሩ ናቸው። በመብራት እፈትሻለሁ ማለቱ፤ አንድም ሰው ሊደበቅና ከእግዚአብሄር ፍርድ ሊያመልጥ በምንም ዓይነት ሥፍራ መደበቅ እንደማይችል ሊያመለክት ነው።
6. በዚያን ቀን የሚሰማው ለቅሶ መራራ ነው፣ የመዓት ቀን ነው፣ የመከራና የጭንቀት ቀን ነው፣ የሁከትና የጥፋት ቀን ነው፣ የጨለማና የጭጋግ ቀን ነው፣ የደመናና የድቅድቅ ጨለማ ቀን ይሆናል። ይህንን ሃሳብ የሚጠቁመን በቁ14 ላይ የምናነበው “በዚያ ጦረኛውም ምርር ብሎ ይጮሃል” የሚለው አነጋገር፤ ጨካኝና ደፋር ነኝ የሚለውን ሰው እንኳን የሚያስጮህና የሚያስለቅስ ቀን እንደሆነ እናያለን።
7. አይነ ስውር ወይም ማየት የማይችል ሰው የሚረግጥበትን እነደማያውቅ ወይም አስተካክሎ ለመርገጥ እንደሚቸግረውና እንደ ሚደናበር ሁሉ፤ እነዚህምን ሰዎች እግዚአብሄር ከጭንቀታቸው የተነሳ የት ልክ እንደ እውር መሄጃቸውንም ሆነ የሚረግጡትን በእርግጠኛነት ሳያውቁ እንደሚጓዙ ማድረጉ ይመስለኛል። በላቸው ሃብት ብዛት እድናለሁ ብለው የሚያስቡትን ሰዎች ነው የሚናገረው?
8. በአንድ በኩል ለእግዚአብሄር መደረግ አለበት የሚባለውን ነገር ሁሉ የሚያደርጉና በቤቱ መመላለሳቸውን፣ መስዋዕት ማምጣታቸውን የማያቋርጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአለምንም ነገር እያከናወኑ በዚያም የሚገኘውን ነገር መልቀቅ የማይፈልጉና አኗኗራቸውን በዓለም ከሚኖሩት ሰዎች ለመለየት የሚያስቸግር ዓይነት ሰዎችን፤ እግዚአብሄርንና ዓለምን አጣምረው ጎን ለጎን ለማስኬድ የሚሞክሩትን ሰዎች በዚህ ክፍል መመደብ እንችላለን።

# ጥናት ሁለት ሶፎንያስ 2፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንዲሰበሰቡና እንዲከማቹ የሚጠራቸውን እነዚህን ህዝቦች "እፍረት የሌላችሁ ህዝብ ሆይ" እያለ ነው የሚጠራቸው። እነዚህ ህዝቦች እንዲሰበሰቡና እንዲከማቹ መጠየቃቸው፤ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ከተነገረውና ከሚመጣው ክፉ ቁጣ ማምለጥ እንዲችሉ የንስሃን እድል እየሰጣቸው ነው።
2. እግዚአብሄር በሞዓባውያንና በአሞናውያን ላይ የተቆጣበት ምክንያት በህዝቡ ላይ ስላፌዙ፣ ህዝቡን ስለሰደቡና በምድራቸው ላይም ስለዛቱ ነው። በእነዚህ ሁለት ነገስታት ላይ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያለውን በቁ9 ላይ ሲናገር፤ ሞዓብ እንደ ሰዶም እንደሚሆንና፤ አሞናውያን ደግሞ እንደ ገሞራ ማለትም፤ ዓረም እንደዋጠው ቦታና እንደ ጨው ጉድጓድ ለዘላለም እንደሚጠፉ ይናገራል። በተጨማሪ የእስራኤል ቅሬታ ደግሞ እነዚህን ነገሥታት እንደሚዘርፉና ምድራቸውንም እንደሚወርሱ ይነግረናል።
3. እነዚህ ሁለት ነገሥታት ትዕቢተኛነታቸውን የገለጹበትን መንገድ ቁ10 ሲናገር፤ "የሁሉን ገዥ የእግዚአብሄርን ህዝብ ሰድበው ዘብተውበታልና፤" በማለት ይነግረናል። እግዚአብሄር በነገስታቱ ላይ ሊያደርግ ያቀደው ነገር ለህዝቡ ደህንናትን ከማስገኘት አልፎ፤ ቁ11 እንደሚነግረን የምድራቱን አማልክት ሁሉ በሚደመሥበት ጊዜ እግዚአብሄር በእነርሱ ዘንድ የተፈራ ይሆናል፤ በተጨማሪም በአካባቢው የሚኖሩትም ህዝቦች እግዚአብሄርን ወደ መፍራትና ለእርሱ ወደ መስገድ ይመጣሉ።
4. በቁ12 እና 13 ውስጥ ደግሞ ለጥፋት እነተዳረጉ የተነገረላቸው መንግሥታት ኢትዮጵያና አሶር ናቸው (ነነዌ የአሶር ዋና ከተማዋ ነች)። በእግዚአብሄር ፊት ትክክለኛ ህይወትን መምራት አንድ ቀን አድርገን ነገ የምንጥለው ነገር እንዳልሆነና፤ በያዝነው የጽድቅ ጎዳና ካልቀጠልን እግዚአብሄር ለዚያ ተጠያቂ እንደሚያደርገን መማር እንችላለን እላለሁ።
5. የበግን፣ የፍየልና የፍጥረት ዓይነት ሁሉ በእርሷ ውስጥ ይመሰጋሉ፣ ጉጉትና ጃርት በግንቦቿ ላይ ያድራሉ፣ ፍርስራሽ በየደጃፉ ይከመራል፣ ከዝግባ የተሰሩ ተሸካሚዎች ይገለጣሉ፣ የተለያዩ እንሣት ጩኸት በየመስኮቱ ይሰማል።
6. በቁ15 ላይ ነብዩ የነነዌን ከተማ፡ ደስተኛይቱ ከተማ ወይም በፈንጠዝያ የታወቀችው ከተማ በማለት ነው የሚጠራት። እግዚአብሄር አንድ ነገር ይሆናል ወይም ይፈጸማል ብሎ አሰበ ወይም ተናገረ ማለት፤ ልክ ነገሩ በተግባር ላይ እንደዋለና ፍጻሜ እንዳገኘ ስለሚቆጠር ነው ነብዩም ወደፊት ይሆናል የሚባለውን ነገር ዛሬውኑ እንደሆነ አድርጎ ያቀረበው።
7. በዚህ ቁጥር ላይ ለትሁታንና የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ለሚፈጽሙት ያንኑ እያደረጉ ያሉትን ነገር ቀጥለው እንዲያደርጉ መምከሩ፤ አይ እኛን ይህ ቁጥና መዓት አይመለከተንም፤ ሁኔታው በሃጥያተኞች ላይ ያተኮረ ስለሆነ እኛ ዘና ብለን መኖር እንችላለን በማለት የተሳሳተ ሃሳብ ውስጥ እንዳይገቡ፤ ነገር ግን በምሳ 4፡18 ላይ እንደሚናገረ የጻድቃን ጽድቃቸው እለት እለት ብርሃኑ እየጨመረ እንደሚሄድ በጽድቅ መንገድ እንዲቀጥሉ ለማበረታታት ነው።

# ጥናት ሶስት ሶፎንያስ 3፡1-20

1. ለዚህች ከተማ የተሰጧት ሶስት ስሞች፡ ዓመጸኛ፣ የረከሰች እና፣ ጨቋኝ የሚሉ ናቸው። ከተማይቷ ዓመጸኛ ነች ሲል በእግዚአብሄር ላይ የምታምጽ ማለቱ ነው፤ የረከሰች ብሎ ሲጠራት ደግሞ በማንነቷ ላይ የሚታየውን ብላሽ የሆነ ባህርይና ህይወት ሲጠቁም፤ ዓመጸኛይቱ በማለት መናገሩ ደግሞ፤ በሰዎች ላይ ማለትም በድሆች፣ በድሃ አደጎችና በማናቸውም አቅም በሌላቸው ላይ የምታደርገውን የጭቆና በህርይ የሚያሳይ ነው። ከማንም እርምት አትቀበልም፣ በእግዚአብሄር አትታመንም፤ ወደ አምላኳ አትቀርብም።
2. በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ላይ የተጠሩት፤ ሹሞች፣ ገዦች፣ ነብያትና፣ ካህናት ናቸው። እግዚአብሄር በህዝቡ ላይ ማተኮሩን ትቶ በመሪዎችና በአስተዳዳሪዎች ላይ ያተኮረበት ምክንያት፤ አገር ሆነ ቤተ ክርስትያን ወይም ሌላ ድርጅትን የሚመሩ ሰዎች ከህዝቡ ተሸለውና ከፍ ባለ ደረጃ ላይ እንዲገኙ ሰውም ሆነ እግዚአብሄር ይጠብቅባቸዋል፤ ምክንያቱም የተቀበሉት አደራና ሃላፊነት በተሻለ ህይወት እንዲገኙ ይጠበቅባቸዋልና ነው። እርሱ ጻድቅ ነው፣ ቅን ፈራጅ ነው፣ በየቀኑም አይደክምም።
3. ከተማይቱ ማን መሆኗን የሚጠቁመን ክፍል ቁ5 ላይ ያለው ሃሳብ ሲሆን፤ ይህም "በእርሷ ውስጥ ያለው እግዚአብሄር" ስለሚል ከተማዋ ኢየሩሳሌም ናት። ቁ7 የመጨረሻውን አረፍተ ነገር ስናነብ "እነርሱ ግን በሚያደርጉት ሁሉ ክፋትንም በመፈጸም እየተጉ ሄዱ።" በማለት ስለሚነግረን፤ በሌሎቹ ላይ ከሆነው ነገር ተምራ መንገዷን ለመቀየር እንዳልሞከረች ነው የምንመለከተው።
4. "በዚያን ጊዜ" የሚለው አጀማመር እኔ እንደሚመስለኝ በቁ8 መጀመሪያ ላይ "ስለዚህ እስከምፈርድበት ቀን ድረስ ጠብቁኝ" ያለውን የእግዚአብሄር የፍርድ ቀን ሲያበቃ እንደሆነ ነው የማምነው። በዚያን ጊዜ እግዚአብሄር ይሆናሉ ብሎ የተናገራቸው ሶስት ነገሮች፡ ሰዎች የእግዚአብሄርን ስም እንዲጠሩ ይሆናል፣ ሰዎች ተስማምተው እንዲያገለግሉ እግዚአብሄር አንደበታቸውን ያጠራል፣ ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የተበተኑት ህዝቦች ለእግዚአብሄር ቁርባንን ያመጡለታል።
5. በዚህ ክፍል እግዚአብሄር የሚናገራቸው ሁለት ዓይነት ሰዎች፤ ትዕቢተኞች ወይም በትዕቢታቸው የሚደሰቱና፣ የዋሃንና ትሁታን በማለት የሚናገራቸው ናቸው። እስራኤል መዘመር፣ እልል ማለትና፣ መደሰት የሚኖርባት ምክንያት፤ እግዚአብሄር አምላቅ ቅጣቷን ስላስወገደ፣ ጠላቶቿን ከእርሷ ስለመለሰ፣ የእስራኤል ንጉስ ከእርሷ ጋራ ስለሆነና ከእንግዲህ ወዲህ የሚያስፈራት ነገር ስለሌለ ነው።
6. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄርንና ህዝቡን የሚያቀርብልን፤ እግዚአብሄር በህዝቡ እጅግ ደስ የሚሰኝበት ጊዜ እንደሚሆን፤ ህዝቡ ደግሞ ባለፈው ህይወታቸው የሆነውን እያሰቡ በሃዘን የሚወጡና የሚገቡ ሰዎች ሳይሆኑ አምላካቸው እግዚአብሄር ከእነርሱ ጋራ ስለሚሆን ልባቸው ሞላ አድርገው የሚወጡና የሚገቡ ሰዎች እንዲሆኑ ያበረታታቸዋል።
7. በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ በአብዛኛው የምናገኘው ሃሳብ እግዚአብሄር ሕዝቡን ሊበትን እንደተነሳ፤ በተለይም ቁ1ድን ስንመለከት "ማንኛውንም ነገር ከምድር ገጽ አጠፋለሁ" በማለት አዋጅ ይናገራል፤ እግዚአብሄር ግን ርህሩህና መሃሪ አምላክ ስለሆነ ህዝቡን ከገባበት ማጥ ውስጥ የሚያወጣበትን መንገድም አስቀድሞ ያዘጋጀ ስለሆነ በሶስተኛው ምዕራፍ ውስጥ ስናይ ህዝቡን መልሶ እንደሚሰበስብ ይነግረናል። ስለዚህም ነብዩ ሶፎንያስ ትንቢቱን ሲጀምር 1፡1 ላይ እበትናለሁ ሲል፤ በመዝጊያው ላይ፤ ማለትም 3፡20 ላይ እሰበስባለሁ በማለት ነው ትንቢቱን የሚዘጋው።
8. ምንም እንኳን እግዚአብሄር በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በተለይም በሶፎ 3፡20 ላይ ህዝቡን ወደ አገሩ እንደሚመልስ የተናገረ ቢሆንም፤ ከዚህ ከተናገረው በረከት ተካፋይ እንዳይሆኑ የወሰነው በትዕቢተኞች ላይ እንደሆነ በቁ11-12 ላይ እናነባለን።